# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 252 መጋቢት 5 2005 ገጽ 1

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ የዜጎች ሂዎት በእብሪተኞች መቀጠፉ እንዲበቃ፣ እንዲያቆም ወያኔን እንታገለው ዘንድ የወጣቱን ህዝባዊ ሃይል የመቀላቀል ጊዜ አሁን ነው።

ሀገራችን መንግስት አልባ ሆናለች፣ ሀገራችን በወንበዴዎች እየተመራች ነው። በሀሰት ወንጀዮች፣ በሀሰት አሳሳሪዎች፣ አዘራፊዎችና ዘራፊዎች፣ አሰቃዮች የነገሱበት ሰአት ላይ ነች ኢትዮጵያ! ስለዚህ ፍትህን ከተቀበረችበት የማውጣት ጥሪ በድጋሜ ይድረሳችሁ። ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የህወሀት መሪዎች በድርጅቱ የወደፊት እጣ ፋንታ ላይ ለመምከር መቀሌ ገቡ

የመለስ ዜናዊ ሞት ከተሰማበት ግዜ ጀምሮ ምሶሶዉ እንደተደረመሰበት ቤት እራሱን ችሎ መቆም ያቃተዉ ህዝባዊ ወያኔ ሀርነት ትግራይ እንዴት ወደፊት መጓዝ እንዳለበትና መጪዉን የኢህአዴግ ጠቅላላ ጉባኤ በተመለከተ ከአባላቱ ጋር ለመምከር በቅርቡ 11ኛ ድርጅታዊ ጉባኤዉን እንደሚጀምር አስታወቀ። በዚህ ከመጋቢት 8 ቀን ጀምሮ ለተከታታይ ሶስት ቀናት መቀሌ ዉስጥ ይካሄዳል ተብሎ በሚጠበቀዉ የግንባሩ 11ኛ ጉባኤው ላይ ለመሳተፍ ነባሮቹ የህወሀት መሪዎች መቀሌ በመግባት ላይ መሆናቸዉን የዘገበዉ የግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢ ገልጿል። በቻይና የኢትዮጵያ አምባሳደር የሆነዉን ስዩም መስፍንን ጨምሮ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ዶ/ር ቴዎድሮስ አድሀኖምና ሌሎችም ከፍተኛ የፌደራል ባለስልጣናት መቀሌ ውስጥ መታየታቸውን የጠቀሰው ዘጋቢያችን የመቀሌ ከተማ “ምን ይመጣ ይሆን” በሚል ፍርሀት መዋጧንና ነዋሪዉ ፊት ላይ ፍርሀት እንደሚነበብ ገልጿል።

የተከፋፈሉት የህወሀት መሪዎች በተከታታይ ስብሰባ ተቀምጠዉ ለ11ኛ ጉባኤያቸዉ የሚሆን አጀንዳ መቅረጽ ተስኗቸዉ ብዙ ከሰነበቱ በኋላ ከሰሞኑ ያለ አጀንዳ ከመሰብሰብ ያዳናቸዉን የግብር ይዉጣ አጀንዳ እንዳዘጋጁ ለማወቅ ተችሏል። መቀሌና ባጠቃላይ ኢትዮጵያ ዉስጥ የህወሀት መከፋፈል በግልጽ እተነገረ ሲሆን ግንባሩ በዚህ እሁድ በሚጀመረዉ 11ኛ ጉባኤዉ ላይ ተአምር ሰርቶ አንድነቱን ካላረጋገጠ ደደቢት ዉስጥ የተጠነሰሰዉ ህወሀት መጨረሻዉ መቀሌ ዉስጥ ሊጀመር ይችላል ብለዉ የሚያምኑ ለህወሀት ቅርበት ያላቸዉ ብዙ የፖለቲካ ተንታኞች እንደገመቱ ዘጋቢያንች ከመቀሌ የላከልን ዜና ያስረዳል።

በአሁኑ ወቅት አንጋፋዋ የመቀሌ ከተማ በአንድ በኩል በህወሀት አርማና በወያኔ ሰንደቃላማዎች ያሸበረቀች ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በየመንገዱ ላይ ጠመንጃ አንግበዉ የሚርመሰመሱት ወታደሮችና መንገዱን ያጣበቡት ወታደራዊ ፒክ አፕ መኪናዎች ከተማዋን አጨናንቀዋታል። ጭራሽ ይህም አልበቃ ብሏቸዉ የወያኔ ካድሬዎች ከቤት ወደ ቤት እየተዘዋወሩ ህዝቡ የጉባኤዉን ማብቃት አስመልክቶ ድጋፉን ለህወሀት እንዲገልጽ በመወትወት ላይ መሆናቸዉን ዘጋበያችን አክሎ የላከልን ዜና ያስረዳል።

## ሙስሊም ኢትዮጵያውያን ተቃውሞአቸውን ቀጥለዋል፣ በትናንትናው እለትም ድምጻቸውን አጠንክረው ሲያሰሙ ዋሉ

ለአንድ አመት ከአድን ወር በላይ ህዝብን ባስደነቀ ስርአት መብታችን ይከበር በማለት የሙብት ማስከበር ትግል በማካሄድ ላይ የሚገኙት ሙስሊም ኢትዮጵያዊያን ይህኑ በጽናት የጀመሩትን ተቃውሞ በመቀጠል በትናንትናው እለት ድምጻቸውን ሲያሰሙ መዋላቸውን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ሪፖርት ገለጸ። የሙስሊሞቹ የተቃውሞ ድምጽ አዲስ አበባን ጨምሮ በበርካታ ከተሞች ጭምር እንደነበርም የደረሰን ዘገባ ያመለክታል።

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት የሙስሊም ኢትዮጵያዊያኑ ተቃውሞ በሻሸመኔ፣ አርሲ፣ ደሴ ፣ ስልጤ እና ሌሎችን ከተሞች ያካተተ እንደነበር ታውቋል።
ሙስሊም ኢትዮጵያውያን አሁንም በማቅረብ ላይ ያሉት ጥያቄ ግልጽና በእስር ላይ የሚገኙት የድምጻችን ይሰማ፣ አመራሮች ይፈቱ፣ አገዛዙ ለጥያቄያችን መልስ ይስጠን የሚሉ እንደነበሩ ታውቋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በአገር ቤት የሚደረገውን ተቃውሞ በመደገፍ በትናንትናው እለት በስዊድን የሚገኙ ሙስሊም እና ክርስቲያን ኢትዮጵያውያን በጋራ የተቃውሞ ሰልፍ ማድረጋቸው ታውቋል።

በትናንትናው እለት በስቶክሆልም ከተማ በኢትዮጵያ ቆንስላ ፊት ለፊት በተካሄደው የተቃውሞ ሰልፍ ፣ አፋኙ የወያኔ አገዛዝ ለዘመናት ተከባብሮ የኖረውን ሙስሊም እና ክርስቲያን ኢትዮጵያውያንን በማጋጨት አገሪቱን ለማጥፋት የሚያደርገውን ሩጫ በጽኑ አውግዘዋል።

በእለቱ "ሁላችንም አቡበክር ነን፣ ሁላችንም ያሲን ኑሩ ነን፣ ኮሚቴዎቻችን ይፈቱ፣ በጅሀዳዊ ሀረካት ሙስሊም እና ክርስቲያን ኢትዮጵያውያን ማጋጨት አይቻልም" የሚሉ መፈክሮች መቅረባቸውን ተያይዞ የደረሰን ዘገባ ያመለክታል።

## የስለላ ተግባርን ቀዳሚ አጀንዳ ያደረገው የወያኔ አገዛዝ የግንቦት7 ንቅናቄን መሰለሉ ተጋለጠ

ኢትዮጵያዊያንን አፍኖና ረግጦ አንድ ለአምስት በተሰኘ አደረጃጀት እስከቤተሰብ የወረደ የስለላ ተግባርን እየፈጸመ ያለው ዘረኛ የወያኔ አገዛዝ የግንቦት 7 ንቅናቄን መረጃ ለማግኘት ከፍተኛ የሆነ የስለላ ተግባር ሲፈጽም እንደቆየ ተቀማጭነቱ አውሮፓ የሆነ አንድ አለማቀፍ የሶፍት ዌር ኩባንያ አጋለጠ።

የወምበዴዎች ጥርቅም የሆነው የወያኔ አገዛዝ በስሩ ለዚሁ ተግባር ያቋቋመው ኢትዮ ቴሌኮም ፊን ስፓይ በመባል የሚታወቀውን ሶፍትዌር በመጠቀም የግንቦት 7 ለፍትህ፣ ለነጻነትና ለዲሞክራሲ መረጃዎችን ሲሰልል መገኘቱን ያጋለጡት ሞርጋን ማርኩዊስ ቦሪ፣ ቢል ማርዛክ ፣ ክላውዲዮ ጋርኔሪ እና ጆን ስኮት በመባል የሚታወቁ ባለሙያዎች ሬይላተን ሲትዝን ላብ በተባለ ዌብሳይት ላይ ባወጡት ጽሑፍ ነው።

እነኝሁ ባለሙያዎች ፊን ስፓይ የግንቦት 7ትን መሪዎች ፎቶግራፍ ወደ ኮምፒዩተር ተጠቃሚዎች በመላክ መረጃዎችን ለኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣናት ለማቀበል መሞከሩን የገለጹ ሲሆን የግንቦት ሰባት ንቅናቄ ኢንተለጀንስ በበኩሉ ፣ የወያኔው አፋኝ አገዛዝ ከድርጅቱ መረጃዎችን ለመውሰድ ተደጋጋሚ ሙከራ ሲያደርግ እንደነበር መረጃዎች እንዳሉት አስታውቋል።

የድርጂቱ መረጃዎች ወደ አፋኙ አገዛዝ እጅ አለመግባታቸውን ያረጋገጠው የግንቦት ሰባት ንቅናቄ ድርጅቱ በስልጣን ላይ ካለው ዘረኛና አፋኝ የወያኔ አገዛዝ ጋር ከፍተኛ የሳይበር ጦርነት ሲያድረግ እንደነበር ም ታውቋል።

ፊን ስፓይ ወንጀለኞችን ለመያዝ ተብሎ የፍትህና የደህንነት ሰራተኞች እንዲጠቀሙበት በሚል መነሻ የተመረተ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን፣ እንደወያኔ አገዛዝ ያሉ አፋኝ መንግስታት ሶፍትዌሩን ተቃዋሚዎቻቸውን በስፋት ይጠቀሙበታል።

## ለሙ ዉስጥ በተቀሰቀሰ የጎሳ ግጭት በርካታ ሰዎች መሞታቸው ታወቀ

ከአዲስ አበባ ጥቂት ኪሎ ሜትሮች ወጣ ብሎ በሚገኝዉና ልዩ ስሙ ለሙ እተባለ በሚጠራዉ ቦታ በኦሮሞና በደቡብ ክልል ተወላጆች መካከል በተቀሰቀሰ ግጭት ለግዜዉ ቁጥሩ በዉል ተለይቶ ባልታወቀ ሰዎች ላይ የሞትና የአካል መቁሰል አደጋ መድረሱን የኢትዮጵያ ሳተላይት ሬዲዮና ቴሌቪዥን ምንጮች ይፋ አደረጉ። ከኢሳት ምንጮች በተገኘዉ መረጃ መሰረት ግጭቱ የተነሳዉ ለሚ እየተባለ በሚጠራው ቦታ በኮብል ድንጋይ ማንጠፍ ስራ ላይ በተሰማሩ የኦሮሞና ደቡብ ክልል ተወላጆች መካከል ሲሆን ባለፈዉ ማክሰኞ ለተቀሰቀሰዉ ግጭት መነሻ የሆነዉ ከዚህ ቀደም በአንዲት የኦሮሞ ተወላጅ ሴት ላይ ጉዳት ያደረሰዉን የደቡብ ክልል ተወላጅ ለመበቀል የኦሮሞ ተወላጆች ተደራጅተው በመምጣት በደቡብ ክልል ተወላጆች ላይ ጥቃት መፈጸማቸውን እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል።

በዚህ ከ10 እስከ 12 ሺ ሰራተኞች እንዳሉበት በሚነገረው የኮብል ድንጋይ ማንጠፍ ፕሮጀክት ላይ እንደዚህ በዘር ጎራ እየለዩ መጣላትና መገዳደል የተለመደና ወያኔ ኢትዮጵያ ዉስጥ ሆን ብሎ የፈጠራቸዉ ችግሮች አካል ሲሆን የአካባቢዉ ፖሊስ ሀይሎች ለይስሙላ ወደ ቦታዉ እየሄዱ ደም መፋሰሱን ለማስቀረት ቢሞክሩም አንድም ቀን ተሳክቶላቸዉ እንደማያዉቅ ለማወቅ ተችሏል። የኢሳት ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ግጭቱን አስመልክቶ የኦሮሚያና የአዲስ አበባ ፖሊስ ሀላፊዎችን ለማነጋገር ተደጋጋሚ ሙከራዎች ቢያደርገም እንዳልተሳካለት ገልጿል።

## ጩኸት እና ዋይታ እንደገና በጋምቤላ...በአማራ

በበደኖ፣ በአርባጎጎ የተጀመረውና በሰው ልጅ ላይ ይፈፀማል ተብሎ በማይታሰበው ኢ- ሰባአዊ ድርጊት ግድያ ተባብሶ ዛሬ ጋምቤላ የጥቃቱ መንደር ባለተራ ሆናለች።

ወደ ኋላ ባለፉት 9 አመታት በጋምቤላ ምድር በወያኔ ጥይት የተገደሉ፣ የተጨፈጨፉ ከ400 በላይ ንጹሃን አኙዋኮችን ማጣታችን ይታወሳል። ያ ሀዘንና ሰቆቃ፣ ጠባሳው ሳይጠፋ ዛሬ ደግሞ ሌላ ዋይታ፣ ግድያ፣ እንግልት፣ ጩኸት በዛው ቦታ በጋምቤላ እንደና እየተሰማ ነው።

ህወሃት/ኢህአዴግ የሚከተለው የዘረኝነት ፖሊሲ አስተዳደር ስልጣኑን እስከጠበቀለት ድረስ ማናቸውንም ዜጋ መግደል፣ማሰር፣ ማባረር እንደሚችል የጋምቤላው ክልል አስተዳደር ደረታቸውን ሞልተው ነግረውናል።

ይህ ዘር ላይ ያነጣጠረው ጭፍጨፋ የጋምቤላን ህዝብ መሬቱንና ቀን ከሌት ደከመኝ ሳይል ያፈራውን ንብረቱን በመንጠቅ፤ የተማረውን የክልሉን ተወላጅ በትውልድ - መንደሩ ስደተኛ፣ የበይ ተመልካች እንዲሆንና እንዲቆጭ እያደረጉት ነው። በተለይም በሀገሩ ምድር በመኖሩ ወንጀለኛ፣ ሽብርተኛ በማድረግ ዜጎች ስለመብታቸው እንዳይጠይቁ የማስፈራራት፣ የወዮላችሁ ዘመቻ ላይ ናቸው ወያኔዎች።

ለሁሉም ኢትዮጵያዊ የሚገርመው: መንግስት የሆነ አካል ቻይና የተበደለን አዳማጭ፣ ፍትህ ሰጭ መሆን ሲገባው፣ ገዳዩም አሳሪውም ፈራጁም መንግስት መሆኑ እንቆቅልሽ ይሆንበታል። ይሄው አካል ቅንጣት ያህል ርህራሄ በሌለው የንጹሃን የሰው ልጅን ክቡር ሂዎት በማጥፋት ይህንንም እንደሚቀጥልበት በራሱ ልሳን የቲቪ መስኮት የተገደሉ ወጣት አኙዋኮችን ሬሳቸውን ከመሳሪያ ጋር በማሳየት እኛ ደም የጠማን ርካሽ አውሬዎች ነን ይሉናል። ከአውሬም አውሬ ሽብርተኞች ናቸው።

በርግጥም ነው ከወደ ባህርዳር ከተማ የክልሉ ተወላጆች በአማራነታችን ምክንያት ከቤንሻንጉል ክልል ተባረርን ለስደት፣ ለእንግልት፣ ለርሃብ ተዳረግን፣ የወላጅ መካን ተበራከተ፣ እኛስ ይሁን ለጋ ህጻናት በምን በደላቸው፣ ሀጺያታቸው ይንገላቱ? እባካችሁ ለወገናችን አልቅሱ፣ ለአማራው አንቡ፣ አቤት ልንል በደላችንን ልናሰማ በሄድን ቤንሻንጉል ሄዳችሁ እንደገና ጠይቁ፣ አይመለከተንም፤ አሁን ግቢውን ለቃችሁ ውጡ ተብለን በፌድራል ተዋከብን፣ ተደበደብን፣ የት እንሂድ? ተቃጠልን የሚል ስቃይም ሰምተናል።

እንግዲህ ወገን የትኛውን ጩኸት፣ የትኛውን ስቃይ ትመርጣላችሁ? በክብር ነክ ስድብ ውርደት መኖር? በአሰቃቂ ጭፍጨፋ ግድያ እጃቸው በደም የተላወሰውን የወያኔን ጎራ ፋከራ ማየትና ከንፈርን መምጠት? ወይስ ለነጻነት ጮራ ፍንጠቃ፣ ለድምጽ አልባዎቹ ዜጎች ድምጽ ለመሆን ከሚታገለው የህዝባዊ ሃይሎች ጎራ መቀላቀል? መልሱን መልሱት።

ግንቦት 7 ንቅናቄ ሀገርን የማዳን ተስፋን አርግዞ ረጅሙን ጉዞ በአንድ ርምጃ ጀምሮታል። የህዝባችን ሰቆቃ በየደቂቃዎች፣ በየሰአታቱ፣ በየቀናቱና ሳምንታቱ የምንሰማው የወገናችን የስቃይ ጣእር የድረሱልን ጥሪ ደወል ለሁሉም የሀገራችን ህዝብና ለነጻነት ታጋዮች ነውና እጅ ለእጅ ተያይዘን ለጥሪው እንድረስ። ከዚህ በላይ ውርደት፣ ስቃይ፣ እንግልት፣ ስደት፣ ሰቆቃ የምናስተናግድበት፣ የምንችልበት አንጀት የለንም። የኢትዮጵያ ወጣት ሆይ በእኛ ይብቃ ብለህ ትግሉን ተቀላቀል።

ዜጎች ፍትህን በሰውነታቸውና በዜግነታቸው ሳይሆን በመደብ ጀርባቸው፣ በዘርና በጎጥ ማንነታቸው በችሮታ የሚሰጥበት የወያኔ ዘመን ላይ ነን። የጋምቤላና የተቀረው ህዝባችን በወያኔ ጥይቶች እየተገደሉ ሲሰደዱ፣ ንብረት አልባ ሲሆኑ፣ ኑሮ ከእጅ ወደ አፍ ሲሆንባቸው፤ በአንጻሩ የወያኔ ጆሌ አጫፋሪ የሆኑ የስርአቱ አገልጋዮች የህወሃት ሰዎች 90 ፐርሰንት በግል ኢንቨስተርነት ታዋቂ ናቸው። ይህ የሚያሳየው የአንድ ፓርቲ ፈላጭ ቆራጭነት አይሎ መንግስት የህዝብ ንብረት ቀማኛ ዘራፊ መሆኑን ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ የዜጎች ሂዎት በእብሪተኞች መቀጠፉ እንዲበቃ፣ እንዲያቆም ወያኔን እንታገለው ዘንድ የወጣቱን ህዝባዊ ሃይል የመቀላቀል ጊዜ አሁን ነው።

ሀገራችን መንግስት አልባ ሆናለች፣ ሀገራችን በወንበዴዎች እየተመራች ነው። በሀሰት ወንጃዮች፣ በሀሰት አሳሳሪዎች፣ አዘራፊዎችና ዘራፊዎች፣ አሰቃዮች የነገሱበት ሰአት ላይ ነች ኢትዮጵያ! ስለዚህ ፍትህን ከተቀበረችበት የማውጣት ጥሪ በድጋሜ ይድረሳችሁ።

ግንቦት 7 ለፍትህ፣ ለነጻነትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ ቀድሞውንም የኢትዮጵያ ህዝብ ፍትህ የማግኘት ተስፋው በወያኔ ተቀብሯል ብሏል። ዛሬ ወያኔ በሀገራችን ፍትህን በመግደል እየዘራ ያለውን አደገኛ መርዝ ለወደፊቷ ኢትዮጵያ እጣ ፈንታ አስቸጋሪ በመሆኑ፤ ላንመለስ ወደኋላ፣ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳንል፣ የፍትህ ቡራኬን ለኢትዮጵያ ህዝብ ለማቃበል፣ ዲሞክራሲን ለማስፈን ወያኔን አስገድዶ ለማስወገድ ትግሉን ጀምረናል።

ወንጀለኞችን ወደፍርድ አደባባይ ለማቅረብ፣ ለድምጽ አልባዎቹ ድምጽ ለመሆን የጥሪ ድምጻችንን ሰምታችሁ ኢትዮጵያዊ የሞራል ግዴታችሁን ትወጡ ዘንድ በራችን ክፍት ነው።ኑ እንታገለው፡፡

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!**

---

## የአውሮፓ ህብረት የልኡካን ቡድን ኢትዮጵያ ዉስጥ የሰብአዊ መብት አያያዝን እንደሚገመግም ተነገረ

ሰላሳ አባላት የሚገኙበት የአውሮፓ የሰብአዊ መብቶች ልኡካን ቡድን ወያኔ በሚገዛት ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ሁኔታ ለመገምገም ወደ አዲስ አበባ እንደሚጓዝ የህብረቱ የዲፕሎማቲክ ምንጮች ገለጹ። ልዑካኑ በኢትዮጵያ ቆይታቸዉ ከተለያዩ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች፣ በእስር ላይ ከሚገኙ ጋዜጠኞችና የሲቪክና የሀይማኖት መሪዎች ጋር ተገናኝተዉ እንደሚመክሩ የሚጠበቅ ሲሆን ግምገማዉ ካለቀና ጭብጥ ከተገኘ በኋላ ግን ህብረቱ በወያኔ አገዛዝ ላይ ስለሚወስደዉ እርምጃ ምንም የተነገረ ነገር የለም።

ከልኡካኑ መሪዎች አካባቢ በተገኘዉ መረጃ መሠረት ጉብኝቱ የሚካሄደዉ በልማት ሽፋን ሲሆን የልኡካኑ ቡድን በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብች አያያዝ እና ችግሮች ዙሪያ ከተለያዩ የአገዛዙ ባለስልጣናት ጋር እንደሚነጋገርም ለማወቅ ተችሏል። ኢትዮጵያ ዉስጥ የዜጎች ሰብዓዊ መብት በቋሚነት ከሚረገጥባቸዉ ቦታዎች አንዱ የቃሊቲ እስር ቤት ሲሆን የአዉሮፓዉ ህብረት የሰብአዊ መብቶች ልኡካን ቡድኑ የቃሊቲ እስር ቤትን ለመጎብኘት ከወያኔ አገዛዝ ባለስልጣኖች ፈቃድ ያግኝ አያግኝ ምንም የታወቀ ነገር የለም። ሆኖም የልኡካን ቡድኑ መሪ ደጋግመዉ እንደተናገሩት ኢትዮጵያ ዉስጥ በእስር ላይ የሚገኙት የፖለቲካና የህሊና እስረኞች ጉዳይ የልኡካን ቡድኑ ከሚያተኩርባቸው ነገሮች መካከል ዋና ዋናዎቹ እንደሆኑ ለማቅ ተችሏል። ከዚህ ቀደም 16 የአውሮፓ ህብረት የፓርላማ አባላት ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ እንዲፈታ ለሀይለማርያም ደሳለኝ ደብዳቤ መጻፋቸው የሚታወስ ነዉ።

---

## የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተብየው ተግዳሮት እንደገጠመውና የኢኮኖሚ እድገት ተብየው ደግሞ ከሁለት አሃዝ እድገት ወደ አንድ መውረዱ በይፋ እየተገለጸ ነው

ገና ከጅምሩ ኢትዮጵያዊያንን ለማደናገርና የሃሳብ አቅጣጫቸውንም ለማስቀየር ታልሞ ለአንድ ሰሞን ህዝብን ሲያደነቁር የነበረው የትራንስፎርሜሽን እቅድ፣ የኋልዮሽ ጉዞ መጀመሩን የዘረኛው አገዛዝ ባለስልጣናት በአደባባይ እየተናገሩና በቁጥጥራቸው ስር ያሉትም የመገናኛ ብዙሃን በይፋ እየዘገቡ መሆኑ ተዘገበ።

የዘረኛው የወያኔ አገዛዝ አቀንቃኝ የሆነው ሪፖርተር ጋዜታ፣ የወያኔው ካድሬዎች ለትራንስፎርሜሽን እቅዱ ወደ ኋላ መጓዝ ጉልህ አስተዋፅ ማድረጋቸውን፣ በተለይም የግብርናው ዘርፍ እድገት ያሳያል ተብሎ ከታቀደለት ውስጥ በ 50 በመቶ የኋልዮሽ መጓዙን ዘግቧል።

ሪፖርተር ጋዜጣ እንደገለጠው የመንግሥት ካድሬዎችና የበታች ቢሮክራቶች በውጭ ኢንቨስተሮች መስተንግዶ ላይ የሚያደርሱት መጉላላት ከፍተኛ ከመሆኑም ባሻገር ኢንቨስት ከማድረግ እንዲታቀቡ እስከማድረስ የሚዘልቅ አስከፊ ሁኔታ እያሳዩ ነው ካለ በኋላ ይህ ድርጊትም ተቀባይነት እንዳለው የወያኔ ባለስልጣናት ማመናቸውን ገልጧል፡፡

በማያያዝም የወያኔው ዘረኛ አገዛዝ የግሉን ዘርፍ ብድር እንዳያገኝ እያደረገ በአንፃሩ ግን እንደ ኤፈርት ላሉት የህዋሃት የንግድ ድርጂቶች ሰፊ ፋይናንስ እያመቻቸ መሆኑን በዚህም ምክንያት እነኝሁ የንግድ ድርጂቶች እስከ 75 በመቶ የሚሆነውን ገንዘብ እየወሰዱ ነው ብሏል፡፡

ሃገር የማጥፋት አጀንዳን አነግቦ ኢትዮጵያን ለሃያ አንድ አመታት ያክል እየገዛ ያለው ዘረኛ የወያኔ አገዛዝ ሃገሪቱን ከፍላ ከማትወጣው እዳ ውስጥ እየዘፈቀና በጣት የሚቆጠሩ ወምበዴ ባለስልጣናትን በሃብት እያምበሸበሸ እንደሚገኝ፣ በስፋት ሲዘገብ መቆየቱ ይታወሳል።

---

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን
የፖስታ ሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916 2003EX Haarlem, The Netherlands

# ከተዘጋው በር ጀርባ

(በጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ)

እነሆ በሶስተኛው በር ተገናኘተናልና አብዝቼ አላማርርም:: ባማርርስ የት እደርሳለሁ? ማነው አዝዙንስ ከስሶ የረታ? ደግሞስ ከመቼ ወዲህ ነው በሀገሬ መሬት ላይ ህግ የበላይ ሆኖ የሚያውቀው? ለማንኛውም የጠፋው ብርሃን በዚህ መልኩ ዳግም ይፈነጥቅ ዘንድ ስለተከፈለው ዋጋ ወይም ውጣ ውረድ ገድል የመፃፍ ፍላጎት የለኝም:: ፍላጎቴ ከባልደረቦቼ ጋር በፀና መንፈስ በጀመርነው ጎዳና እንተም ዘንድ የመንግስትን አፈና አውግዛችሁ የሞራል ድጋፍ ለሰጣችሁን ኢትዮጵያውያን፤ እንዲሁም የአለም አቀፍ የፕሬስ ነፃነት ተሟጋች ተቋማት ላሳያችሁት አጋርነትና ተቆርቋሪነት፣ በሀገሬ ላይ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ይሰፍን ዘንድ ዋጋ በከፈሉና እየከፈሉ ባሉ ወንድምና እህቶቼ ስም ልባዊ ምስጋናዬን ማቅረብ ነውና-ቺርስ ለነፃነታችን!

...አሁን በዚህ አምድ ላነሳው ወደ አሰብኩት ርዕሰ ጉዳይ ልንደርደር::
የዘንድሮ ጥር እና የካቲት ወራት ለየት ባለመልኩ በሁለት ክስተቶች ላይ ትኩረት ሰበው ነበር ያለፉት:: አንዱ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን በደቡብ አፍሪካ በተካሄደው ሃያ ዘጠነኛው የአፍሪካ ዋንጫ ላይ ያሳየው ድንቅ እንቅስቃሴ ሲሆን፤ ሌላኛው ደግሞ ገዥው ኢህአዴግ የሚመለከት ነው:: የእኔ የዛሬ ትኩረትም ሁለተኛው ነውና ጉዞ ወደ አጀንዳችን::

### እንደመግቢያ

በኢትዮጵያ የፖለቲካውን መዘውር የጨበጡ ገዢዎች በሙሉ አራምደዋለሁ ብለው በይፋ የሚያውጁትን ርዕዮተ-ዓለም ለማስረፅ የሚሄዱባቸው መንገዶች የየራሳቸው መለያ (ገፅታ) እንዲኖራቸው ያደርጋቸዋል:: በተለይ ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር በርካታ መለያዎች አሉት::

በቀደሙት ስርዓታት ከማይታወቁ እና የኢህአዴግ መለያ ከሆኑት መካከል ለ‹‹ዶክመንተሪ ፊልም›› ያለው ፍቅር ዋነኛው ነው:: ለዚህም ይመስለኛል ‹‹አስገኘሁት›› ከሚለው የኢኮኖሚ እድገት አንስቶ፣ የፖለቲካ ተቀናቃኞቹ ላይ እስከሚፈፅመው ቅጥ-ያጣ ጉልበተኝነት ድረስ መከራከሪያው በጉምቱ ፖለቲከኞቹ የሚዘጋጀው ዶክመንተሪ ፊልም ብቻ የሆነው:: ህገ-መንግስት፣ የተለያዩ ህጎች፣ አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች... በስርዓቱ መዝገበ ቃላት ላይ ቦታ ኖሯቸው አያውቅም::

በሀገር ጉዳይ እና በመብት ጥያቄ ላይ ‹‹የነቃ ተሳትፎ ያደርጋሉ›› ወይም ‹‹ሊያደርጉ ይችላሉ›› ብሎ የጠረጠራቸውን እልፍ-አእላፍ የኦሮሚያ ተወላጆችን በኦነግ ስም ለመምታት በርካታ ዶክመንተሪ ፊልም በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ተሰተናግዷል:: እነ እስክንድር ነጋን እንዳሻው ከሚቆጣጠረው ፍርድ ቤት ተሽቀዳድሞ በሽብርተኝነት ለመወንጀል የቀረበውን ‹‹አኬልዳማ›› የተባለውን ቀሽም ፊልምስ ከቶስ ማን ይረሳዋል? የእስልምና ሀይማኖት መንፈሳዊ መሪዎች ላይ ለተመሰረተው የሀሰት ክስ ማስረጃ ‹‹ይሆነናል›› በሚል ቀመር ተዘጋጅቶ፣ ባለፈው ወር እንድንመለከተው የተደረገው ‹‹ጀሃዳዊ ሀረካት›› ፊልምም ስርዓቱን ራሱ ምን ያህል እንዳከሰረው ከማንም የተሰወረ አይደለም (በነገራችን ላይ ‹‹መለስ እንደወታደራዊ ሳይንስ መሀንዲስ›› የተሰኘው ዶክመንተሪ ፊልም አቶ መለስን በእጅጉ በተጋነነ ስብዕና አፍርሶ ለመስራት የተደረገ ፕሮፓጋንዳ እንደሆነ ለሰራዊቱ አመራር እጅግ ቅርብ ከሆኑ ሰዎች ሰምቻለሁ:: በተለይ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት መለስ ስለነበራቸው ሚና አስመልክቶ የተተረከው ክፍል የፊልሙን ቅሽምና በሚገባ የሚያሳይ እንደሆነ ነው ያነጋገርኳቸው ያረጋገጡልኝ:: እዚህች ጋ የምናገኘው ተጨማሪ አስቂኝ ነገር ሰራዊታችን ሻዕቢያን ከድንበራችን በኃይል ለማባረር ከምርጥ የጦር ታክቲክ /ብልሀት/ ይልቅ የሰው ኃይልን በብዛት መጠቀሙ ተደጋግሞ ሲተችበት የቆየ እውነት ሆኖ ሳለ ‹‹መለስ የጦር ጠበብት በመሆኑ በነደፈው ስልት ነው ኤርትራን ያሸነፍነው›› የምትለዋን የፊልሙን ‹‹ውዳሴ-ዘመለስ›› ስናደምጥ ነው)

የሆነ ሆኖ ‹‹ጀሃዳዊ ሀረካት›› የተሰኘውን ፊልም ስመለከተው እንደተለመደው ተራ ከመሆኑም በላይ እርስ በእርስ በሚጣረሱ ጭብጦች የተሞላ ሆኖ አግኝቸዋለሁ (በዚህ ፊልም ላይ ከእነ ማስረጃዬ በሌላ ጊዜ እመለስበታለሁ):: ይሁንና ለነገ ሊተው የማይገባው አንድ ጉዳይ ግን አለ:: ይኸውም በመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት በሚኒስትር ዴኤታ ማዕረግ ምክትል ሀላፊ የሆነው አቶ ሽመልስ ከማል ከሁለት ሰዓት ዜና በኋላ በታየው ‹‹ጀሃዳዊ ሀረካት›› ፊልም ላይ ያልተካተተ፣ ነገር ግን በአኩለሌሊቱ የኢቲቪ ስርጭት ወቅት በድንገት የታየውን (ኡስታዝ አቡበከር ሁለት እጆቹ በካቴና ታስረው መርማሪዎቹ ለሚጠይቁት ጥያቄዎች መልስ ሲሰጥ የሚያሳየውን) ፊልም በተመለከተ ለ‹‹ኢትዮ ቻናል›› የሰጠው ቃለ-መጠይቅ ነው:: ለቁም ነገር ባይሞሉ ወሬዎች ከተሞላው የአቶ ሽመልስ ምላሽ ውስጥ እስኪ አንዷን እንምዘዝ::

የመንፈሳዊ መሪዎቹ ጠበቃ ተማም አባቡልጉ ዶክመንተሪው በፍርድ ቤት ስራ ጣልቃ የሚገባ መሆኑን ጠቅሶ እንዲታገድለት ያቀረበው አቤቱታ በፍርድ ቤቱ ተቀባይነት አግኝቶ እንዲታገድ ቢወሰንም፣ የፍርድ ቤቱ ፕሬዝዳንት ግን ተፈፃሚ እንዳይሆን ተከላክለዋል:: በኋላም የአገዛዙ የፕሮፓጋንዳ ማሽን ኢቲቪ ፊልሙን መልቀቁ ወንጀል መሆኑን መነሻ በማድረግ ጠበቃው በተለያዩ ሚዲያዎች ላሰማው ተቃውሞ የሰጠውን አፀፋ ማለቴ ነው:: ሚኒስትር ዴኤታው:-

‹‹...ፕሮፓጋንዳ ታስቦበት የተወሰነ እውነትን ደፍቀህ ሌላውን መርጠህ የምትፈልገውን ዓላማ እንዲከተልልህ ለማድረግ ህብረተሰቡ ላይ የአስተሳሰብ ጫና ለማድረስ ነው›› ካለ በኋላ፣ ‹‹...ይሄ ነጭ ቅጥፈት ነው::...›› ሲል በራሱ መንግስት ላይ ምፀት የምትመስል ውንጀላን ተናገረ (መቼም ይህች ፍረጃ ደርጉ ተቀናቃኞቹን ይከስበት ከነበረው ‹‹ነጭ ሽብር›› የተገለበጠች ሳትሆን አትቀርም)::

ይህ የአቶ ሽመልስ ምላሽ እንኳን ከሚያገለግለው ስርዓት ውጭ ላለው ታዛቢ ቀርቶ፣ ለራሱ ድርጅት ካድሬም ቢሆን ከልጆች ጨዋታ ያለፈ ትርጉም ሊኖረው እንደማይችል አይጠፋውም ብዬ አስባለሁ:: ስለእውነት ደፈቃም ሆነ ስለነጭ ውሸት የምር እንነጋገር ከተባለም የአቶ ሽመልስ እና የጓዶቹ ብቻ በርካታ መጽሐፍትና በርካታ ዶክመንተሪዎች እንደሚወጡት አልጠራጠርም:: ስርዓቱ እውነትን በምን ያህል ደረጃ እንደሚደፍቅም ለማወቅ በአንድ ወቅት አለም አቀፍ የፕሬስ ነፃነት ተቆርቋሪ ተቋማት ‹‹የኢትዮጵያ መንግስት ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋን፣ ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬን፣ ጋዜጠኛ ርዕዮት ዓለሙን፣ ጋዜጠኛ የሱፍ ጌታቸውን... አስሮ ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብትን ደፍጥጧል›› በሚል ላቀረቡት ተቃውሞ፣ አቶ ሽመልስ አይኑን በጨው አጥቦ ‹‹እስክንድር ነጋን በጋዜጠኝነት አናውቀውም›› ያለውን ማየት ብቻ በቂ ይመስለኛል (እስክንድር በተለያዩ ጊዜያት ከስድስት ያላነሱ በስሩ የሚያስተዳድራቸው ጋዜጦች እንደነበሩት ይታወሳል):: እንዲሁም አቶ በረከት፣ አቶ መለስ ያደረበት ህመም ‹‹ነፍስ-ውጪ፣ ነፍስ ግቢ›› ላይ እንዳደረሰው በይፋ አምኖ ሳለ፣ ምክትሉ አቶ ሽመልስ ‹‹ይሄ የኢሳት እና የእሳት ወሬ ነው›› ሲል ማጣጣሉም የ‹‹ነጭ ቅጥፈት››ን ሰፈር አመላካች ይመስለኛል:: ‹‹መንግስት በአደባባይ ይዋሽ ዘንድ በህግ ተፈቅዷል›› ካልተባለ በቀር::

### ከተዘጋው በር ጀርባ...

የድህረ መለስ አስተዳደርን ተከትሎ በህወሓት እና ኦህዴድ ውስጥ ‹‹ያደፈጠ ፖለቲካ›› እንዳለ በርካታ ተንታኞች መግለፃቸው ይታወሳ:: በተለይ ደግሞ ህወሓት ዛሬም ድረስ ከአናት ካሉ አመራሮቹ በቀር፣ በየትኛውም ደረጃ በሚገኙ አባላቱ ላይ ሳይቀር ህቡዕ ገብቶ የሀገሪቱ ቀጣይ ‹‹መልክ›› ምን መምሰል አለበት? የሚለውን የቤት ስራ ለማጠናቀቅ ደፋ-ቀና እያለ ነው:: ፓርቲው እመራቸዋለው ከሚላቸው ዜጎቹ፣ ይጠብቁኛል ከሚላቸው ደጋፊዎቹና ይሞቱልኛል ከሚላቸው አባላቶቹ ጀርባ ሆኖ ዛሬም እንደተረበሸ ሾልከው የሚወጡ ድምፆች ያሳብቃሉ:: ይህንን መከራከሪያ የካቲት 16 ቀን 2013 ዓ.ም የታተመው ‹‹The Economist›› መፅሄትም ‹‹Ethiopia's new leadership is practicing hero-worship›› በሚል ርዕስ ባስነበበው መጣጥፍ ‹‹Jockeying among the elite has been kept behind firmly closed doors. In public it espouses business as usual. (በልሂቃኑ መሀከል ያለው መተጋገል በጥብቁ ከተዘጋው በር ጀርባ እየተካሄደ ቢሆንም፣ በአደባባዩ ግን ነገሮች በነበሩበት እየቀጠሉ እንደሆነ ለማስመሰል እየተሞከረ ነው) ሲል አጠናክሮታል:: እናም ከመወያየ አዳራሹ ደፍ እንዳያልፉ የተደረጉትን ፖለቲካዊ አጀንዳዎች በጨረፍታ እንያቸው::

### ፩

በሀገሪቱ መጻኢ ዕድል ላይ እንደዋነኛ ስጋት ተደርጎ የተወሰደው ‹‹በህወሓት ውስጥ ተፈጠረ›› የተባለው ልዩነት ነው:: የልዩነቱ አንጓ ምክንያት ተደርገው ከሚቀርቡት መካከል ቀልቤን የሳቡት:- መለስ ‹‹ብቸኛው ሰው›› (Strong man) እንዲሆን የትሮይ ፈረስ ሆነው አገልግለዋል ተብለው የተፈረጁ የአመራር አባላት መኖር፣ ‹‹መለስ ከፖለቲካውም ሆነ ከኢኮኖሚው ጨዋታ አግልሎን ነበር›› በሚል ቅሬታ ስር የተሰባሰቡ ባለስልጣናት፣ ‹‹የትግራይ ህዝብን ከሌላው ብሄር የሚነጥል ስልት በመከተል ተሳስተናልና ማስተካከል አለብን›› የሚል አቋም የያዙ አመራሮች መምጣት፣ አውራጃዊነት፣ ዝምድናና ጋብቻ የፈጠረው ቡድንተኝነት... በመጀመሪያው ረድፍ ይቀመጣሉ:: ከእነዚህ በተጨማሪም ‹‹አቶ መለስ በህይወት በነበረበት ጊዜ ድርጅቱን ደካማ በማድረጉ፤ የእርሱ ህይወት ካለፈ በኋላ ስልጣን ከድርጅታችን እንዲወጣ ምክንያት ሆኗል›› በማለት ጥቂት የአመራር አባላትን እና የታችኛው ካድሬን በፓርቲው ላይ የማነሳሳት ሙከራ ባደረጉት አቦይ ስብሃት ነጋ እና በተቀረው የህወሓት አመራርም መካከል አደጋ ሊያደርስ የሚችል ልዩነት ተፈጥሮ እንደነበር ይነገራል::

የሆነ ሆኖ በአቦይ ስብሀት ነጋ ፊት-አውራሪነት እየተንቀሳቀሰ ነው ተብሎ የሚታሰበው የህወሓት ግንባይ፣ በእነአባይ ፀሀዬና ደብረፅዮን መስመር ከተሰለፈው ብዙሀኑ አመራር ጋር የነበረውን ልዩነት ባለፉት ሁለት ወራት በምን መልኩ እና በማን ሽምጋይነት ለድርድር ቀርበው ስምምነት ላይ እንደደረሱ ግልፅ ባያደርጉትም፣ መግባባት ላይ መድረሳቸውን አንድ የድርጅቱ የቅርብ ሰው አረጋግጠውልኛል:: ይህንንም ተከትሎ ስብሃት ነጋ፣ አቶ መለስ ከአደባባይ ከራቀ ጀምሮ ከ‹‹ፋጡማ›› እና ‹‹በቀለ›› ጋር በማነፃፀር ሲያጣጥሉ የነበሩብትን አካሄድ አርመው (በድርጅቱ ቋንቋ ግለ-ሂስ አድርገው) እንደአብዛኛው የኢህአዴግ አመራር ‹‹የመለስ ራዕይን ለማስፈፀም...›› የሚሉ ቃላቶችን በንግግራቸው መጀመሪያ ሲጠቀሙበት ተስተውለዋል:: (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የኢትዮጵያን የፖለቲካ፤ የኤኮኖሚና የሐይማኖት ችግሮች የዳሰሰ ህዝባዊ ስብሰባ ዋሺንግተን ዲሲ ዉስጥ ተካሄደ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የሚፈጽማቸዉን ግፎች በሰፊዉ የዳሰሰና አያሌ የመፍትሄ ሀሳቦችን ያካተተ ህዝባዊ ስብሰባ አሜሪሪካን ዋና ከተማ ዋሺንግተን ዲሲ ዉስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያለዉ የዲሲ፤ የቨርጂንያና የሜሪላንድ ነዋሪ ኢትዮጵያዉያን በተገኙበት ባለፈዉ እሁድ መካሄዱን እዚያዉ ዋሽንግተን ዉስጥ የሚገኙ የግንቦት ሰባት ዘጋቢዎች በላኩልን ዜና ገለጹ። በዚህ የእስልምናና የክርስትና እምነት አባቶች፤ ምሁራን፤ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎችና የሰብዓዊ መብት ታጋዮች በተሳተፉበት ህዝባዊ ስብሰባ ላይ ተገኝተዉ ንግግር ካደረጉ ታዋቂ ኢትዮጵያዉያን ዉስጥ ብጹዕ አቡነ ፊሊጶስ፤ ዝነኛዉ ጋዜጠኛ ሳድቅ አህመድ፤ ከእልምና እምነት አመራር አካባቢ ሼክ ከሊድና አቶ ነጂብ መሐመድ፤ ከምሁራን ዶ/ር አክሎግ ቢራራና አቶ ፈቃደ ሸዋቀና የሚገኙበት ሲሆኑ ስብሰባዉን የመሩት ደግሞ ወ/ት ሂሩት ልብሰወርቅ ናቸዉ።

በዚህ ስምንት የተለያዩ ተናጋሪዎች ንግግር ባደረጉበት ስብሰባ ላይ ከአንድ አመት በላይ ዕድሜ ያስቆጠረዉ የኢትዮጲያዉያን ሙስሊሞች ትግል በሽብረተኝነት የመፈረጁ ጉዳይ፤ የታሪካዊዉ የዋልድባ ገዳም ጉዳይና ጥንታዊቷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤ/ክርሲቲያን ለሁለት የመከፈሏ ጉዳይ የስብሰባዉን ተሳታፊዎች በብዛት ያወዩዩ ዋና ዋና አርዕስቶች ነበሩ። ይህንን ስብሰባ ከብዙ ዋሺንግተን ዲሲ አካባቢ ከተደረጉት ስብሰባዎች ልዩ የሚያደርገዉ የአገራችን ሁለቱ ትልልቅ ሐይማኖት መሪዎች መድረክ ላይ ጎን ለጎን ተቀምጠዉ ይህ የምናደርገዉ ትግል የኢትዮጵያ ህዝብ ለመብትና ለነጻነት የሚያደርገዉ ትግል ስለሆነ እስላምና ክርስቲያን ብለን ሳንከፋፈል በጋራ እንታገል የሚል ጥሪ ማስታለፋቸዉ ነዉ። አቡነ ፊሊጶስ ወያኔ ክርስቲያንና እስላም እያለ ለመከፋፈል የሚያደርገዉን ጥረት ማክሸፍ ብቻ ሳይሆን የወንድሞቻችንን ትግል በሽብርተኝት መፈረጁን ነግበኔ ነዉና አጥብቀን ልንቃወመዉና ልንዋጋዉ ይገባል ሲሉ ሼክ ከሊል ደግሞ ኢትዮጵያ ዉስጥ እንደ ህዝብ የምንዝዘዉም ነጻ የምንወጣዉም አንድ ላይ ነዉ፤ ሙሰሊሙ ነጻ ሳይወጣ ክርስቲያኑ ነጻ መሆን አይችልም ወይም ያሻንን ያክል ብንታገል ክርስቲያን ወንድሞቻችን እየተገዙ እኛ ሙስሊሞች ብቻችንን ነጻ ነን ማለት አንችልም ብለዋል።

በስብሰባዉ ላይ የተገኙ ቁጥራቸዉ በርካታ የሆነ ኢትዮጵያዉያን በስብሳዉ እጅግ የረኩ መሆናቸዉን ጥያቄ በመጠየቅና አስተያየት በመስጠት ያሳዩ ሲሆን በስብሰባዉ ላይ በርካታ ሴቶች እህቶቻችን ተገኝተዋል። አብዛኛዉ ተሰብሳቢና ተናጋሪዎች እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ይህንን ከአንድ አመት በላይ ዕድሜ ያስቆጠረዉን የሙስሊም ወንድሞቻችን "ድምጻችን ይሰማ" የሚል ትግል እንዲቀላቀልና አገሩን ኢትዮጵያን ከወያኔ ዘረኝነት ማዳን እንዲችል ተዳጅቶ መታገል እንዳለበት አበክረዉ አስጠንቅቀዋል። ከዚህ በተጨማሪ የስብሰባዉ ተሳታፊዎች እንደዚህ አይነት ህዝብን የሚያሳትፍና የህዝብን አንድነት የሚያጠናክር ስብሰባ በየግዜዉ እንዲደረግና የስብሰባ ተሳታፊዎችም በአድማጭነት ብቻ ሳይሆን በታጋይነትም እንዲሳተፉ ጥሪ አድርጓል።

## ከተዘጋው በር ጀርባ

. . . (ከገጽ 3 የዞረ)

ከዚህ በግልባጩ ደግሞ ሁሉም የህወሓት ሰዎች ሙሉ በሙሉ መግባባት ላይ እንዳይደርሱ ያስቸገራቸው ሌላኛው ደግሞ የቀድሞዎን ቀዳማዊት እመቤትንና ተከታዮቿን ፍላጎት ተመስርተው የሚነሱ ጥያቄዎችን በቀላሉ መመለስ አለመቻሉ ነው:: የእነወ/ሮ አዜብ መስፍን ጥያቄ የሁለቱንም ፖለቲካዊ ጥግቶች አርከቶ፣ በህወሓት ውስጥ የአንበሳውን ድርሻ በመያዝ አብዛኛውን አመራር ከጎኑ ማሰለፍ ከቻለው ቡድን ጋር ለመቆም አሁንም ጊዜው ገና ይመስላል።

በእርግጥም በቢሊዮን የሚቆጠር ንብረት ያለው የኤፈርት ስራ-አስኪያጅነት መንበር ዛሬም በአዜብ እጅ መሆኑ፣ የበላይነት ያለውን የህወሓት አመራር ምቾት ቢነሳ አስገራሚ ላይሆን ይችላል:: ይህን ጉዳይ ለጥጠን አዜብ መስፍን በሚያዚያ ወር ለሚካሄደው የአዲስ አበባ አስተዳደር ምክር ቤት እጩ ሆና ከመቅረቧ ጋር ካያያዝነው፣ ምናልባትም የኤፈርት ስራ አስኪያጅነት ቦታዋን በከንቲባነት ለመለወጥ ስምምነት ላይ ደርሳ ሊሆን ይችላል ብለን እስከ መከራከር ልንደርስ እንችላለን::

እንደተጨማሪ መላ-ምት የአዜብን ወደ ከንቲባነት የማምጣት የፓርቲውን መግፍኤ ከሌላ ጫፍም ማየት የሚቻል ይመስለኛል:: ይኸውም የሴትዮቱ ፖለቲካዊ ስብዕና ከመለስ የቀድሞ ማንነት፣ እንዲሁም አሁን እየተባለ ካለው ‹‹ባለራዕይነቱ›› ጋር መተሳሰሩን ጠንቅቆ የሚያወቅው ህወሓት በቀጣዩ የ2007 ዓ.ም የፌደራል ምርጫን በሚቹ ስብዕና ስም መወዳደሩ ማትረፍ፣ ያለማትረፉን ለማረጋገጥ የወ/ሮይቱን ከንቲባነት የፕሮፓጋንዳው ሙቀት መለኪያ ለማድረግ አስቦ ሊሆን ይችላል የሚል ነው:: ማለትም የአዲስ አበባ ነዋሪ ‹‹የመለስ ሀሳብ ሳይከለስና ሳይበረዝ›› ለምትለዋ ወ/ሮ አዜብ የሚሰጠው ምላሽ፣ ፓርቲው በቀጣዩ ምርጫ የመለስን ስም በመሸጥ ለመወዳደር የሚያደርገውን ዕቅድ መወሰኛ ሁነት ይሆነዋል::

ሌላው ፈተና ሆኖ ዛሬም ድረስ የዘለቀው ‹‹እነስዬ ይመለሱ›› የሚለው የታችኛውን ካድሬ ግፊት፣ ህወሓት ሊሆን እንደማይችል አሳምኖ ማስቆም አለመቻሉ ነው:: የዚህ ሀሳብ አቀንቃኞች መከራከሪያ አድርገው የሚያቀርቡት ‹‹በ1993 ዓ.ም ህወሓት ለሁለት መከፈሉን ተከትሎ ጠንካራው አመራር ሲባረር፣ በምትኩ ብቁ የሆነ ተተኪ ስላልተፈጠረ ድርጅታችን ተዳክሟልና የቀድሞ አመራሮቹ ወደ ድርጅቱ ተመልሰው ፓርቲያችን መጠናከር አለበት›› የሚል ነው:: የሀሳቡ ደጋፊዎች ‹‹የተሻለ አመራር የሚሰጥ ብቃት ያለው ሰው ባለመኖሩ ነው ስልጣኑ ከህወሓት እጅ የወጣው›› የሚል እምነት አላቸው:: ይሁንና ህወሓት አሁን ባለበት ደረጃ ይህንን ጥያቄ ማስተናገድም ሆነ ማንሳት እንደማይቻል አቋም የያዘ ይመስላል:: በአናቱም ‹‹መለስ እንደወታደራዊ ሳይንስ መሀንዲስ›› የሚለው ዶክመንተሪ ፊልም እንዲቀርብ የተደረገው ‹‹የድርጅታችን አንጎልና ልብ መለስ ብቻ ነበር›› የሚል የጎንዮሽ መልዕክት በማስተላለፍ ‹‹እነ ስዬ ይመለሱ›› የሚለውን ጥያቄ ለማምከን በሃሳቡ ነቃፊዎች የተቀመረ ነው ብሎ መከራከር ይቻላል::

፪

በኦህዴድ ውስጥ የተፈጠረው ቀውስም እንዲሁ መፍትሄ አላገኘም:: ምናልባትም ኦህዴድ ከተመሰረተ ጀምሮ እንደ ድህረ-መለስ ዘመን አይነት በስብሰባ የመወጠር ታሪክ አጋጥሞት የሚያውቅ አይመስለኝም:: ኦህዴድ መፍትሄ እንዳያገኝ እንቅፋት ሆነው ከተከሰቱበት ችግሮች መካከል ዋነኛው ከእግሩ ራሱን ችሎ የቆመ ይምሰል እንጂ፣ አናቱ በህወሓት ውስጥ መገኘቱ እንደሆነ ይነገራል:: ይኸም ከእነአባዱ ፀሀዬና ከእነአዜብ መስፍን ልዩነት የሰረፀ ይመስለኛል:: በጥቅሉ የኦህዴድ አመራር አሰላለፍ አባዱላ ገመዳ፣ ኩማ ደመቅሳ፣ ሙክታር ከድር... የመሳሰሉት ከጠቅላይ ሚንስትር ኃ/ማርያም ደሳለኝ ጀርባ ሆኖ የፖለቲካ ስልጣን በያዘው ጠንካራው የህወሓት አመራር ስር ሲሆን፣ አስቴር ማሞ፣ ሶፊያን አህመድ፣ አለማየሁ አቱምሳ... ደግሞ ወደ እነ አዜብ መስፍን ቡድን የማዘንበል አዝማሚያ ይታይባቸዋል:: (በኦህዴድ ውስጥ የቡድን አባቶች እነዚህ አመራሮች ናቸው) ሁለቱም (የህወሓት ቡድኖች) ኦህዴድን ‹‹ችግር መውጫ›› ማድረግ መፈለጋቸው ነው ድርጅቱን መረጋጋት የነሳው:: በተጨማሪም የኦህዴድ አመራሮች ከህወሓት ሁለቱ ቡድኖች ጋር ለመሰለፍ መስፈርት ያደረጉትም የድርጅታቸው መለያ የሆነውን ከረጅም ጊዜ ጀምሮ መንደርተኝነትን እና የጥቅም ግጭትን ለመዳኘት፣ በህወሓት ሰዎች የተያዘውን አቋም ነው:: በአናቱም የህወሓት የታሪክ ንባብ እንደሚነግረን በድርጅቱ ውስጥ ልዩነቶች ሲከሰቱ በአሸናፊነት ለመውጣት የትኛውንም ህግ መጣስ እና ሀገራዊ ጥቅምን አሳልፎ መስጠት አዲስ ነገር አለመሆኑን ነው (ቀጣዩ የኦሮሚያ የፕሬዝዳንት ወንበርም ለኦህዴድ አመራር ማማለያ ሆኖ ቀርቧል)

፫

የድህረ-መለስ ኢህአዴግ ከፖለቲካው ጋር ለተያያዙ ችግሮቹ እልባት ለመስጠት ከህግ ውጪ መስራትን እንደ ስልት የያዘው ይመስላል (የሶስቱ ምክትል ጠቅላይ ሚንስትሮች ሹመት አንዱ ማሳያ ነው):: ስርዓቱ የጠቀስኳቸውን የውስጥ የቤት ስራዎቹን በአግባቡ ያለማጠናቀቁ መንግስታዊ ተቋማትን በማቀዛቀዝ ሀገሪቷን እየጎዳት እንደሆነ ከውስጥም ከውጭም እየተሰማ ነው:: ከላይ የጠቀስኩት የዘ ኢኮኖሚስት መፅሄት ዘገባም ‹‹ከመለስ ውጪ ህልውናቸውን ማስቀጠል የተሳናቸው›› እና ‹‹ግራ የተጋቡ›› ያላቸው መሪዎች ኢኮኖሚውን ነፃ የማድረጉን ጉዳይ ከሚቀጥለው አገራዊ ምርጫ ወዲያ አሻግረውታል ሲል አመራሩን አብጠልጥሏል:: ሌላኛው ተያያዥ ጉዳይ የሀገሪቱ ህዝባዊ ተቋማት የእርስ በእርስ የስራ ግንኙነት በመለስ ዘመን በነበረው ልክ እንኳን መሄድ ያለመቻሉ ነው:: ለዚህም ማስረገጫ የሚሆነው በቅርቡ የወጣው ትውልደ ኢትዮጵያውያን የውጪ ዜጎች በጥብቅና እንዳይሰማሩ የሚያግደው አዋጅ ነው:: በጉዳዩ ላይ የነጋገርኳቸው አንድ የህግ ባለሙያ እንደሚሉት ስለጉዳዩ የፍትህ ሚንስቴር ባልስልጣናትንም ሆነ የጠቅላይ ሚንስትሩን ፅ/ቤት ሲጠይቁ ‹‹እንዲህ የሚባል አዋጅ መውጣቱን አናውቅም›› ሲሉ መልሰውላቸዋል:: እነዚህ ሁለት ተቋማት የማያውቁት አዋጅ እየወጣ ነው ከተባለን ሀገሪቱን ማን እየመራት ነው? የሚለው ጥያቄ አሁንም መጠየቅ የሚችል ይመስለኛል:: እናም በየተቋማቱ ውስጥ ያሉ ዝቅተኛና መሀከለኛ አመራሮች ‹‹የሚመራንና ሪፖርት የምናደርግለት አጣን›› የሚል ጉሩምርታ እያሰሙ ነው::

### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

**መካከኛ ሞገድ:-** በ 358 MB, በ 837 kHz
**አጭር ሞገድ:-** በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድህረገፃችን፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታሳውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

### ውድ አንባቢዎቻችን

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org